# የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
# UNITED ETHIOPIAN DEMOCRATIC FORCES (UEDF)

## አመድ በጹቄት ሲስቅ!

ኢትዮጵያን በዓለም ቀደምት ከሚባሉት ጥቂት አገሮች መኻል የሚያስመድባት ሥርዓተ-መንግሥት መሥርታ፥ ድንበሮቿን አስከብራ፥ የባሕር በሯን ጠብቃ በሽዎች ለሚቆጠሩ ዘመናት የኖረች ሉዓላዊት አገር በመሆኗ ነው። ይኸ እውነታ የአቶ መለስ ዜናዊ ቡድን ሥልጣን ላይ እስከተቆናጠጠ ድረስ ሳይሸራረፍ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ እንደኖረ ታሪክ ብቻ ሳይሆን አሁን ያለው ትውልድ ጭምር የሚገነዘበው ሃቅ ነው። ይኸ ደምና አጥንት ሲከፈልበት የኖረውና ዓለም ያወቀው አገራዊ ቅርስ ዛሬ በአቶ መለስ አሸባሪ ቡድን የአገዛዝ ዘመን ተደፍሮና ተሸራርፎ ኢትዮጵያውያንን ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያን ታሪክ የሚከታተሉ ወዳጆቻችንንና ታዛቢዎችን ያሳዘነ ነገር ሆኖ ይገኛል።

ጥቂት ዓመታት ወደኋላ መለስ ብለን ሻዕቢያ አሥመራን የተቆጣጠረበት ፲፱፻፺፩ ዓ/ምን ስንቃኝ ፸፭ ሺህ ኢትዮጵያውያን ንብረታቸውን እየተዘረፉ ከኤርትራ ሲባረሩ የአቶ መለስ ቡድን የዜጎቹን መብት መረገጥና መንገላታት ከምንም ሳይቆጥር የሻዕቢያ ስም መጥፋቱ ከንክኖት በኢትዮጵያውያን ላይ የደረሰውን በደል ሲያስተባብልና የሻዕቢያን ግፍ ሲሸፍን ተገንዝበናል። ይኸ ቡድን ለሻዕቢያ ያለውን ታማኝነት ሲያረጋግጥ ኤርትራን በዓለም ፲፫ኛ የቡና አምራች አገር ተብላ በዓለም-አቀፍ ገበያ እንድትመዘገብ ያደረገውን የኢትዮጵያ ሃብት ዘረፋ ያከናወነ ከሃዲ ቡድን ነው።

የነአቶ መለስ አሸባሪ ቡድን በአገርና በሕዝብ ላይ እያደረሰ ያለው ክህደትና በደል መረኑን እየለቀቀ በመሄዱ ለኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን ለዓለም ማኅበረ-ሰብም አሳስችል ባለበት ወቅት "አመድ በጹቄት ይስቃል" እንዲሉ ይኸ ሃፍረተ-ቢስ ቡድን ለአገር ሉዓላዊነትና ለሕዝብ መብት መከበር ከባድ መስዋዕትነት በመክፈል ላይ ያሉትን ታጋዮች በአገር ክህደት ወንጀል ሲከስ ይደመጣል። አገርና ሕዝብን በመክዳት ዓለም ያወቀው የመለስ ቡድን በቅርቡ የበርካታ አገር-ወዳድ ዴሞክራት ኢትዮጵያውያንን ስም ዝርዝር ያዘለ ፅሑፍ በመበተን በአገር ክህደት ወንጀል ይጠየቃሉ ብሎ ዘግቧል። ክሱ የመለስ ቡድን ክህደቶች በተጨባጭ ከላይ በተጠቀሰው መልክ ተዘርዝሮ ባይገለፅም እንዲያው በደፈናው የብዙ ፖለቲካ ድርጅቶችንና የሲቪክ ማኅበራትን እንደዚሁም የግለሰቦችን ስም በመጥቀስ በአገር ክህደት ወንጀል ይጠየቃሉ ይላል። ይኸ አሸባሪ ቡድን ከከሰሳቸው የኢዴኃኅ አመራር አባላት መካከል፥ 1ኛ. አቶ ፋሲካ በለጠ የኅብረቱ ሊቀ-መንበር 2ኛ. አቶ አረጋዊ በርሄ የኅብረቱ ም/ሊቀ-መንበርና የኅብረቱ አውሮጳ ጽ/ቤት ሃላፊ 3ኛ. ዶ/ር ነገደ ጎበዜ የኅብረቱ አመራር አባል ይገኙበታል። እነዚህ ታጋዮች ለአገር ሉዓላዊነትና ለሕዝብ መብት መከበር ሲሉ የግል ኑሮአቸውን ወደ ጎን ትተው ሌት ተቀን የሚታገሉ ከመሆናቸው በተጨማሪ አሥራ-አራት ድርጅቶችን ያቀፈው ኢዴኃኅ ሙሉ እምነት ጥሎባቸው ትልቅ ሃላፊነት ላይ ያስቀመጣቸው ውድ ኢትዮጵያውያን ናቸው። አብረዋቸው የተጠቀሱ ኢትዮጵያውያንም እንዲሁ የመለስ ቡድን እንደሚዘባርቀው ሳይሆን በአገር-ወዳድነታቸውና በዴሞክ-ራትነታቸው የሚታወቁ ዜጎች ናቸው።

ይኸ የነ አቶ መለስ ጭፍን ውንጀላ " ሳይቀድሙኝ ልቅደም" በሚል የጮሌዎች ፈሊጥ ብቻ ታይቶ የሚዘለል አይደለም። ሌላ መሰሪ መልዕክትም ያዘለ ነው። እንደሚታወቀው በስደት የሚኖሩት አያሌ ኢትዮጵያውያን አገራቸው ውስጥ ገብተው ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መፈጠር በሚደረገው ሕዝባዊ ትግል ሊካፈሉ ይፈልጋሉ። የኢትዮጵያ ሕዝብም

ዋና መሥሪያ ቤት (Main Office)
ፖ.ሣ.ቁ./P.O.Box 73246
Washington DC 20056-3246,U.S.A
ስልክ/Tel. 202-291-4217;
ፋክስ (Fax) 202-291-7645

ኢትዮጵያ (Ethiopia)
ፖስታ ሣ.ቁ./P.O.Box
Addis Abeba,Ethiopia
ስልክ/(Tel.) 251 1530945
ፋክስ/Fax:251150942

አውሮጳ (Europe)
Jonathan Str. 82
2524 JJ The Hague,
Netherlands
Tel/Fax 31 70 394 6132

ሆነ የዓለም-አቀፉ ኅብረተ-ሰብ በዚህ የዜግነት መብት ጉዳይ ላይ ትኩረት ሰጥቶ የመለስ ቡድን እገዳውን እንዲያነሳ ያላሰለሰ ተፅዕኖ እያደረገ ነው። ይኸ ተፅዕኖ ለውጤት በቅቶ ሁሉም አገር-ወዳድና ዴሞክራት ኢትዮጵያዊ አገሩ ውስጥ ገብቶ ለዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት ግንባታ፥ ለሕግ የበላይነት፥ ለሰብዓዊ መብቶች መከበር የተለመውን አስተዋጽዖ ተግባር ላይ የሚያውል ከሆነ፥ የሥልጣን ዕድሜው የሚያበቃለት ለመሆኑ ግልጽ የሆነለት የመለስ ቡድን ትግሉን ለማጨናገፍ ያቀደው ሌላ የቀቢፀ-ተስፋ ተንኮል መሆኑ ነው።

ግራም ነፈሰ ቀኝ የአቶ መለስ ቡድን ሥልጣን ከያዘ ቀን ጀምሮ አገር ቆርሶ ሲሸጥ፥ የዜጎችን መብት ረግጦ ሲያስር፥ ሲገድል፥ ሲያፍን፥ ሕዝቡንም ለዘግናኝ ድህነት፥ በሽታና መቅሰፍት በመዳረግ የሚታወቅ ለመሆኑ አሁን አገሪቱና ሕዝባችን ያሉበት ሁኔታ እራሱ ምስክር በመሆኑ በአገር-ወዳዶችና ዴሞክራቶች ላይ የሚውጠነጠነው ውንጀላ እንዲያው "አመድ በዱቄት ሲስቅ" ብሎም ሲሳለቅ ብለን ብናልፈው በቂ ይመስለናል። የዚህ አሸባሪ ቡድን ተጠያቂነትንና እውነትን አጥብቆ በመፍራት ጥፋትን ወደ ሌላ ለመላከክ መሞከር የማይሆን "ግመል ሰርቆ አጎንብሶ" ዓይነት መታከት ነው። የእራስን ክህደት በሌሎች ላይ በማላከክ ሥልጣን ላይ ለመሰንበት የሚደረገው ከንቱ ሙከራ ሁሉ የሕዝቡን ማዕበል መግታት የማይችልና እንዲያውም የአገር-ወዳዶችንና የዴሞክራቶችን የትግል ወኔ የሚያጎለብት መሆኑን ከወዲሁ ግልጽ ማድረግ እንወዳለን።

እውነትን ወደ ሌላ ለመላከክ መሞከር ከተጠያቂነት አያድንም!
በማጭበርበር ሕዝባዊ ቁጣን ማምለጥ አይቻልም!!
ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት

ጥር ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ/ም